ብንሄድ ይሻላል ...

አንድ ሰሞን ይህ ቃል ፋሽን ሆኖ መጥቶ ነበር። ዱንያ ያደከመቻቸው እና ተሰፋ የቆረጡ ውጣቶች እንደዋዛ የጀመሩትና ሕይወታቸዉን ለማጥፋት የተጠቀሙበት ቃል ነው። ቃሉ በአንዲት ሴት ተጀመረና በቃል ደረጃ በስፋት፤ በተግባር ደግሞ ጥቂቶች ዘንድ ደረሠ። ብዙዎች በቀልድም በቁምነገርም "ብንሄድ ይሻላል" ብለው ሶሻል ሚዲያው ላይ ፖሰቱ። ውጣቶች ፋሽንን መከተል ይወዳሉ መቸስ። ፋሽኑ መልካም ቢሆን መከተሉ ባልከፋ። ግና አላህ የማይወደው ነገር ሆነና ተቸገርን።

ሁላችን ያለን አንዲት ነፍስ ባለቤትነቷ ለአላህ ሱብሐነሁ ወተዓላ ነው። የፈጠራት እሱ ነው። ባለቤቱም እሱ ነው። እንደፈለገ ሊያረጋት የሚገባዉም እሱ ነው። ሊያኖራትም ሆነ ሊገድላት ሙሉ መብት ያለው እሱ ነው። ነፍስ የሱ ሰሪት በመሆኗም አላህ እኔ የፈጠርኩትን ነፍስ ያላግባብ አትግደሉ ብሎናል። የራስን ነፍስ ማጥፋትንም ከልክሏል። ነፍሴ ናትና የራሴን ነፍስ እንደፈለግኩ አደርጋለሁ የማለት መብት የለንም። የሌላ አካል በሆነው ንብረት ላይ የይገባኛል ጥያቄ እንደማናነሳው ሁሉ አላህ በፈጠራት ነፍስ ላይ ምንም መብት የለኝም። በርግጥ አላህ የፈጠራትን ነፍስ ያጠፋ ከ የቂያማ ቀን ትልቅ ቅጣት ይጠብቀዋል።

ሰዎች መሞታቸው ላይቀር ነገር ነፍሳቸዉን ለማውጣት አላህን መሸቀዳደማቸው ተገቢ አይደለም። የዚህ ዓለም ፈተና በሁሉም ላይ ነዉና ባገኘኝ ከባድ ችግር ምክንያት ተሰፋ በመቁረጥ ሞትን መመኘት የለብንም። "በደረሰበት ችግር ምክንያት አንዳችሁም ሞትን አይመኝ።" ብለዋል ነቢያችን ሶ.ዐ.ወ.። አላህ ፈጥሮት የረሳው አንድም ባርያው የለም። የማያልፍ ነገር የለም፤ ላያልፍ የመጣ ነገርም የለም። መከራም ችግርም ማዕበል ነው ያልፋል። ፈተና ሲበዛ ምንዳም ይበዛል። በነፃ አንፈተንምና ሞትን ከመመኘትና በራስ ላይ ጥፋት ከመጥራት ይልቅ አርቆ ማሰቡ ነው የሚያዋጣው። እስኪያልፍ ድረስ ቡትዕግስትና ተስፋ መጠበቅ ራሱ ዒባዳ ነው። አላህ የወደደልንን ነገር ሁሉ መውደድም አላህን ከመውደድ ነው ። ስለሆነም አምላኩን የሚወድ አሱ የማይወደዉን ነገር አያደርግም ። ማንን ደስ ይበለው ብላችሁ ነው ራሳችሁን የምታጠፉት? አህአ። ከዐይናቸው እንድትጠፉ የማይፈልጉ ወዳጆቻችሁንስ ለምን ታሳዝናላችሁ። በራስ ጊዜ ወስኖ መሄድ መልካም አይደለም። አላህ ያኖረንን ያህል አኑሮ በራሱ ጊዜ ቢወስደን ይሻላል። አላህ ሆይ መኖር ለኛ መልካም እስከሆነ ድረስ አኑረን። መሞት የሚሻልልን ከሆነም አንተው ዉሰደን።

ደወል (1)

ወዳጆቼ! በዚህች በኖርኳት የዱንያ ሕይወቴ የገባኝ ነገር ቢኖር ሁሌም ዲኔን አጥብቄ መያዝ እንዳለብኝ ነው። ሁሌም በፍፁም መልኩ ወገኖቼ መሆን ያለበት ለዲኔ ነው። ከሁሉም ነገር በፊት ዲኔን ማስቀደም እንዳለብኝ ነው። ሁሉም ነገር የሚመጣው ከዲን በኋላ ነው።

ወዳጄ ሆይ! ተከፋን፣ ተገፋን ብለን የምንገባባቸው ብዙ ነገሮች ረጅም ሳንጓዝ ባልሆነ ነገር ሲጠለፉ እናያለን። የፖለቲካ ብዙው ክፍሉ የጠራ አይደለም። የሆነ ጊዜ ላይ በየዋህነት እና በቁጭት አውነት ይዘናል ብለን ልንቀላቀለው እንችላለን። ግና በደል ስላንገሸገሸን ብቻ የገባንበት ትግል ብዙ ጥልፍልፍ ዉስጥ ሲወድቅ እናያለን። ነገሩ እንደተመኘነው አይሆንልንም። በጠበቅነው መልኩ አይሄድም። ያሰብነው አይሳካልንም። የኒያችንና የፍላጎታችን አይሰምርም።

ወዳጄ ሆይ! ብዙው የፖለቲካ ትግል ላዩ ሲታይ ጥሩ ይመስላል እንጂ ዉስጡ ጭቃ ነው። ብዙ አጁ በሊድልዎ የተሸፈነ ነው። ሰፊ ጎኑ በጥቅም፣ በድብቅ ዓላማ እና በሥልጣን የተበከለ ነው። ቢደል አለው፤ ሴራ አለው፣ አድልዎ አለው፣ ዘረኝነት አለው፣ አውነትን ማለባበስ አለው፣ ድብቅ አጀንዳ አለው፣ ኢፍትሃዊነት አለው፣ ዲንን መጉዳት አለው፣ ወንድምን መበደል አለው፣ አህትን ማጣት አለው፤ ያላግባብ ነፍስ ማጥፋት ሊኖረው ይችላል፣ ከዲን ወንድም ያሳክራል፣ አዝነትን አጥፍቶ መጪካከንን ያወርሳል። ከዚህም አልፎ ቀልብን ያደርቃል፣ ከሚባዳ ያርቃል፣ ሶላትን ያስተዋል፣ አኺራን ያስረሳል።

ስለዚህ አደራ ወዳጆቼ! በማንኛዉም መልኩ ስለወገን በደል ትግል ከመጀመራችን በፊት ጉዳዩን በደንብ እናስብቡት፤ በሚገባ እናጢነው። በጥልቀት እንመርምረው። ጥቅምና ጉዳቱን እንለያ። ነገሩ ወደፊት ምን ሊሆን እንደሚችልም እናስተነትን። አርምጃችን ከሰሜት ይልቅ በሰሌት ይሁን። አርግጥ ነው በግል እና በግልፅ የምናውቃቸዉን ግፎች አጥብቀን እንቃወም፣ ለማስተካከል መታገል አለብን። በአደባባይም እናውግዝ። ግና ያልጠሩ አና ድብቅ አጅንዳ ከሞላባቸው ትግል መሳይ ትግሎች እንጠንቀቅ፣ ሰዉን ከመበደል እንራቅ። ዲኑም አጠራጣሪ ከሆነው ነገር አጠራጣሪ ወዳልሆነው ነገር አዘንብል ይል የለ። በተለይ ከሰው ልጅ ደም ትልቅ ጥንቃቄ እናድርግ። ሙአሚን የሰው ደም አስካላገኘው ድረስ ዉስጡ ሰላም ነው። አላህ መልካሙን ሁሉ ያመላከተን፤ ወደቀናው መንገድ ይምራን።

እኔ ያንተው ድሃ ...

ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ.) በተጣሉ ሰዎች መካከል ለ.ገላግሉ ገብተው አንደኛዉን ያጠቃዉን ድንገት በቦክስ ሲሙቱት በእጃቸው ሞተ:: በሰሀተት የሰው ነፍስ በእጃቸው ላይ በመጥፋቱ ምክንያት ግፈኞች አንዳይገድሏቸው ፈርተው ከግብፅ ሸሽተው መድየን ምድር ዘለቁ::

ነቢ. ሙሳ ዐ.ሰ. ሁሉን ነገር ለአላህ ጥለው ጌታዬ ወደመራኝ ይምራኝ ብለው ተሰደዱ:: አካሄዳቸው ነፍሳቸዉን ለማዳን ብቻ ስለሆነ ባዶ እጃቸዉን ነበሩ። መድየን ምድር ሰው አያውቁ፣ አገር አያውቁ፣ ሥራ የላቸው፣ ዘመድ የላቸው።

እዚያ እንደደረሱ ባይተዋርነት፣ ብከነትና ብቸኝነት አጠቃቸው። ከዚያም ወደ ወንዝ ወረዱ። ሁለት ሴቶች ከብቶቻቸውን ዉሃ ለማጠጣት ሲቸገሩ አዩ። ወርደው አጠጡላቸው:: ይሆንን መልካም ሥራ ሠሩና ወደ አንዲት የዛፍ ጥላ ሥር ተጠጉ። እጃቸዉን አነሱና ዱዓ አደረጉ።

' እጉተ ወደኔ ከምታወርደው መልካም ነገር ድሃ ነኝ።" አሉ። ርቧቸው፣ ደክሟቸዉም ነበርና የአላሆን ሲሳይና በረከት ለመኑ:: ቸርነትህ ሰፊ ሆኖ አያለ ለኔ አልደረሰኝምና ከሰፈው ችሮታህ ለግሰኝ። አሉ:: አላህ የነቢያቸዉን ዱዓ ወዲያዉኑ ሰማ:: የባይተዋሩን ሰው ተማጽኖ ተቀበለ:: መልካም ከሠራላቸው ሴቶች መካከል አንዷ በተረጋጋ ሁኔታ እየተራመደች ተመልሳ ወደርሷ መጣች:: የነቢይ ልጅ ነበረች:: አላህ ሲልከ አንዴት ላከ አይባልም መቸስ:: "አባቴ ስለሠራህልን መልካም ነገር ዉለታ ሊከሰህ ብሎ እየጠራህ ነው::" አለቻቸው:: ነቢዩ ሙሳ ዐ.ሰ. ወደተጠሩበት አቀኑ። ከልጃገረዶች መካከል አንዷ አባቴ ይህ ሰው ጠንካራ እና ታማኝ ሰው ነዉና ቅጠረው አለች:: አባትም ለተወሰኑ ዓመታት አገልግለኝና ከሁለቱ ልጆቼ አንዷን አድርሃለሁ አሏቸው:: ነቢ ሙሳም ተስማሙ:: አላህ ከመልካም ቤተሰብ አሰጠጋቸው። ከዚያው ቤት መጀመርያ ምግብ፣ ከዚያ መጠለያ፣ ከዚያም ትዳር አገኙ::

አንድን መልካም ሥራ ከሠሩ በኋላ ይህን ዱዓ ማድረግ ይወደዳል ይላሉ ዑለሞች፣ "ረቢ. አ.ንኒ ሊማ አንዘልተ ኢለይየ ሚን ኸይሪን ፈቂር::"

ወዳጆቼ! ለሰው ያደረጋችሁትን መልካም ዉለታ አትቁጠሩ፣ እንዲህ እንዲያ አድርጌለት አትበሉ፤ ለአላህ ብቻ ንገሩና ዘወር በሉና በሥራችሁ ወደርሱ ተቃረቡ::

ኢያረፍን...

ከቅጣት ሁሉ ከባዱ ቅጣት በኃጠኣት ላይ መዘውተር፤ መንፈሳዊነትን መራት፥ ኢማንን መገፈፍ፤ ከአላህ ጋር የማውራትን ጥፍጥና አለመቃደል፥ ቁርኣንን መርሳትና ኢስቲግፋርን ችላ ማለት ነው። ዱንያ ላይ ከቀልብ ይልቅ በሰዉነት ላይ የሚደርሰው በሽታ ቀላል ነው። (ኢብኑል ጀውዚ)

****

ወዳጆቼ! ጥሩ ሰው ነፍሱ ጥሩ ናት። እኛም ጥሩ ሰው ለመሆን እየታገልን ነው።

****

ላ ተሕዘን ኢንነላህ መዐና ...

- ከወዳጅነትና ጓደኝነት ሁሉ እጅግ የሚያስቀናው እና ምርጡ የነቢያችን ሶ.ዐ.ወ. እና የሰይዳችን አቡበከር ረ.ዐ. ነው።

- አርሳቸው ለርሱ፤ አርሱ ለርሳቸው እውነተኛ ሷሒብ ናቸው። በደጉም በክፉዉም ጊዜ ሁሉ አልተለያዩም አብረው ነበሩ፤

- ነቢዩም (ሶልሏሁ ዐለይህ ወሰለም) ጠላቶቻቸው በሚያሳድዷቸው በዚያች የቀውጢ ጊዜ፤ ካሁን ካሁን ተያዝን ብሎ ሲጋትና ሐዘን ለገባው ወዳጃቸው አቡበከር "አትዘን፤ አላህ ከኛ ጋር ነው።" አሉት።

- በርግጥ አላህ ከርሱ ጋር የሆነ ሰው ሐዘንም፤ ፍራቻም፤ ስጋትም ሊወርሰው አይገባም።

- በርግጥ በደህናው እና በሰላሙ ቀን ሁሉ ሰው ወዳጅ ነው። ችግር እና መከራ ደግሞ እውነተኛ ሷሒብ እንደሆነ መለያ ነው።

ወዳጆቼ! ሕይወት ከባድ ናት። አይዞህ ባይ እውነተኛ ወንድሞችና አህቶችን ሲኖሩ ግንን ከብደቷ ይቀላል፤ ችግሯም ይገራል። ጥሩ ወንድም ሸክምን ይጋራል፤ ሐዘንን ይካፈላል፤ መከራን ያሻግራል። አንዳንድ ወንድሞቼ እኔው ናቸው። አነርሱን ላገኛቸው ራሴን ያገኘሁ ያህል ይሰማኛል ።

ሷሒቦቼ አብሽሩ።

መጀመርያኑ አለመጀመር ...

ወደ ሞጥፎ ነገር መገለለቅ ከፍ ብሎም መልመድና መላመድ ለሙአሚን ሞቱ ነው። ሙአሚን መጥፎ ነገርን በሩቁ ይጠየፋል። አብዝቶ ይጠላል። ከሞጥፎ ነገሮች መካከል ዋናው እና ትልቁ ኃጢአት ነው። ወደ ኃጢአት የተጠጋና በዙርያው የሚሽከረከር፤ ጥብቅ ማሳ አካባቢ ከሚግጥ እንሠሣ ጋር ይመሳሰላል። ሁለቱም አንድ ቀን ከልከል ወደሆነዉና ወደታጠረው መስክ መግባታቸው አይቀርም። በመሆኑም ምንም አልሆነም ብሎ መዘናጋት ዋጋ እንደሚያስከፍል መታወቅ ይኖርበታል። ከመዳፈርም መራቁ ይመረጣል። ለአንድ አማኝ ኃጢአትን መጀመሩ ነው ከባዱ ነገር: : አንድ ሙአሚን መጠንቀቅ ያለበትም ይህንኑ ነው። አላህ ከከለከለው ድንበር ላለመድረስ እስከመጨረሻው መታገል ግድ ይለዋል። መጥፎ ሱስን የጀመረ ሰው ይለምደዋል። የለመደም ሱሱ ይሆነዋል። ተሸንፎም ከፅድቅ ጎዳና ይርቃል። ኃጢአት ደራሽ ወንዝ ነው እያሳሳቅ ይወስዳል።

እናም ወዳጄ ... ኃጢአትን ላለመጀመር ታገል። ከጀመርከው እየተለመደ፤ እየቀለለ፤ ሰጢነት እየሆነ፤ እየጣፈጠ፤ ኃጢአትነቱ ጭምር እየተረሳ ይመጣል። ስትለምደዉም በፊት እንደተራራ ታየው የነበረ ግዙፉ ወንጀል ኖርማልና ተራ ነገር ይሆናል። የሐላል እና ሐራም ድንበሩና መስመሩ እስኪጠፋህ ድረስ ትሆናለህ። እዚያ ደረጃ ላይ ከደረስክ በርግጥ ተጎድተሃል። ሞተሃል። ከስረሃል። ጠፍተሃልና አሪ ብለህ አልቅስ፡

ወዳጄ ሆይ! ወደ ኃጢአት መንደር ላለመግባት ከመጀመርያው ጀምሮ መታገል ግድ ነው። ከመጀመርያው እይታ ጀምሮ ታገል። ከመጀመርያው ማዳመጥ ጀምሮ ታገል። ከመጀመርያው ትዉዉቅ ጀምሮ ታገል። ከመጀመርያው መደዋወል ጀምሮ ታገል። ጉዳዩን ችላ አትበል፤ ምንም አይሆንም፤ ምንም አያገኘኝም፤ አይገጥመኝም አትበል። ንቀህና አቅልለህ አትመልከት፤ አልወድቅም ብለህ አትከተል። ራስህን ያዝ፤ ስሜትህን ተቆጣጠር፤ ሥራህን ዝምግም፤ አካሄድህን መርምር፤ መዳረሻህን አስተዉል፤ መውደቂያህ ምን ሊሆን እንደሚችል አርቀህ አስተንትን። ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንላቸው እንዲህ ይላሉ:- "ከሰዎች ሁሉ የተሟላው ሰው ሁሌም መታገልን የሚያበዛው ነው፤ትልቁ ትግልም ነፍስን መታገል፤ ስሜትን ማሸነፍ ሸይጧንን መርታት ነው::"

ወዳጆቼ! ኃጢአትን ከመዳፈር አንፃር አሁን ያለሁበትንና በፊት የነበርኩበትና ሁኔታዬን ሳመዛዝነው አንዳንድ ጊዜ እኔው ስለመሆኔ እጠራጠራለሁ። ረበና ይስቱር።

አብሸር ወንድሜ

የሰው ልጅ ብቻዉን አንድ ሰው ነው፤ ከሰው ጋር ሲሆን ግን ብዙ ነው። የአያም ልጅ ሁሉ በአንድም ይሁን በሁለት መልኩ ድጋፍ ፈላጊ ነው። አብሸር የሚለዉን ሰው አጥብቆ ይፈልጋል። ሰው አይዘህ አትስጋ፣ የሚሆነዉን ሁሉ አብረን እንሆናለን ባይ ወንድም አስኪያገኝ ድረስ ዱንያ ከወዲህ ወዲያ የምታላጋው ግዑዝ ነው። ብቻዉን የሚንቀሳቀስ ባተሌ ነው።

መልካም ወንድም ከአላህ የተሠጠ መልካም ሀብት ነው። መልካም ወንድም ለወንድሙ አለሁልህ ይለዋል። ሀሳብ ሲገባው ምን ሆንክ ብሎ ይጠይቀዋል፣ ሲወድቅ ያነሳዋል፣ ሲሰበር ይጠግንዋል፣ ሲደክም ይደግፈዋል፣ ሲደነግጥ ያረጋጋዋል፣ ሲጠፋ ይዘይረዋል፣ በዲኑ ጉዳይ ያስታዉሰዋል፣ በዱንያ ላይ ይመክረዋል። ወንድምህ ነኝ አይዞህ! አህትህ ነኝ ከጎንህ አለሁ .. የሚል ወንድም አህት ማግኘት መታደል ነው።

ወንድም አላህ የሚልከው ሪዝቅ ነው፤ አህት ከአላህ የተላከች ፀጋ ናት። መልካም ወንድም ወይም አህት የተሠጠ ሰው ብዙ ነገር ተሠጥቷልና ስለዚሁ ጉዳይ አላህን አብዝቶ ያመሰግን። የሆድህን የምታወራው፣ ሚስጢርህን የምታካፍለው፣ ዓላማህን የምትነግረው፣ አብሮህ የሚያነባ፣ ሐዘንህን የሚረዳ፣ ጉዳትህን የሚካፈል፣ ሳትናገር የሚያነብህ፣ ቃል ሳታወጣ የሚያደምጥህ፣ ሳትተነፍስ የሚገነዘብህ ወንድም አህት ማግኘት መታደል ነው። ወንድምነት ምላስ አይደለም ተግባር ነው፤ አህትነት ወሬ አይደል ለቋም ነው፣ ወዳጅነት ልፈፋ አይደለም ድርጊት ነው። ሰዎች ባገለሉህ ጊዜ ያቀረበህ፣ በከፋህ ጊዜ ምን ሆንክ ያለህ፣ ሥምህን ሲያጠፉ የተከላከለልህ ... እሱ ነው ወንድም ማለት።

ወንድም ማለት እንደ አቡበከር ነው። የነቢዩ ሶ.ዐ.ወ. ሚስጢረኛቸው ነበር። በመልዕክተኛነታቸው በመጀመርያ ያመነባቸው እርሱ ነበር። አውነተኛ መሆናቸዉን በርግጠኝነት ይመሰክር ነበር። ቁረይሾች ሲመታቸው ለርሣቸው ብሎ ተደብድቧል። በሰደት ጊዜ ባልደረባቸው ሆኖ መዲና ዘልቋል። አማካሪያቸው ነበር። ገንዘብም ሆነ ሌላ ነገር ሲቸግራቸው ያግዛቸው ነበር። ወንድም ማለት እንዲህ ነው። በአስፈላጊ ቦታ ላይ ሁሉ ቀድሞ የሚገኝ። ሰው ያሳለፋቸዉን ከባባድ ቁናት ሊረሳ ይችላል፤ እነዚያን ከባባድ ቁናት እንዲያልፍ ያደረጉትን ወንድም አህቶች ግን ፈጽሞ አይረሳም።

ሰባሐል ኸይር ወዳጆቼ! አላህ መልካም ወንድም አህት ይለግችሣሁ።